MCPS MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
www.montgomeryschoolsmd.org
MARYLAND

Malcolm Baldrige National Quality Award
2010 Award Recipient

ፌብሩዋሪ 2014

ውድ ወላጆች/ሞግዚቶች

በሚመጡት ሳምንቶች፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች በአመታዊው የስቴት ፈተናዎች አፈፃፀም ይሳተፋሉ። እንደምታውቁት፣ በMaryland School Assessment (የሜሪላንድ ት/ቤት ግምገማ) (MSA) እና በPartnership for Assessment of Readiness for College and Careers (ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት ግምገማ ሽርክና) (PARCC) አማካይነት በመዳበር ላይ ባሉት በአዲሶቹ ፈተናዎች መካከል በሽግግር ላይ እንገኛለን።

በማርች ወር መጀመርያ ላይ፣ ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የሚገኙት አብዛኛዎች ተማሪዎቻችን፣ በዚህ አመት ለመጨረሻ ጊዜ በሚከናወነው፣ የምንባብና የሂሳብ MSA ይወስዳሉ። ቢሆንም፣ በነሲባዊ ዘዴ የተመረጡ የተማሪዎች ናሙና በእያንዳንዱ ት/ቤት "ተግባራዊ ሙከራ ፈተና" ("field test") ተብሎ በሚጠራ የአዲሱ PARCC ግምገማዎች ሙከራ ላይ ይሳተፋሉ። የነዚህ ተማሪዎች ወላጆች በት/ቤት በኩል እንዲያውቁ ይደረጋል። የተግባራዊ ሙከራ ፈተና ትርጉም ያለው የግምገማ ግንባታ በጣም አስፈላጊ አካል ነው፣ ውጤቶቹንም የሚመጣው አመት ፈተናው ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት የፈተናው አዘጋጆች ማሻሻያ ለውጦች ለማድረግ ይገለገሉባቸዋል።

በዚህ አመት የሜሪላንድ ስቴት MSAን ተግባራዊ ማድረጓ ተምሪዎቻችንን ወይም ት/ቤቶችን ይጠቅማል ብየ አላምንም፣ ብዙ ወላጆች፣ መምህራን፣ እና የካባቢና የስቴት መሪዎችም ተመሳሳይ ስሜት አላቸው። MSA በአለም አቀፍ ደረጃ ወደተመሰረተው የጋራ ዋነኛ የስቴት መመዘኛዎች (Common Core State Standards) በምንሸጋገርበት ወቅት በመወገድ ላይ ካሉት ከቀድሞ የስቴት መመዘኛዎች ጋር የተያያዘ ነው። በMontgomery County፣ እንዲሁም በስቴቱ በሞላ፣ ብዙ ሰዎች ከወቅታዊ መመዘኛዎች ጋር በሚገባ ካልተያያዘ እና ተማሪዎቻችንና ት/ቤቶች በውነቱ እንዴት በመስራት ላይ እንዳሉ ትርጉም ያለው መረጃ በማይሰጥ አንድ ፈተና ላይ ጠቃሚ የትምህርት ግዜ በመጥፋቱ ቅሬታቸውን ገልፀዋል። የሆነ ሆኖ፣ ስቴቱ MSAን ስራ ላይ እንዲያውል ፌዴራል ህግ ስለሚጠይቅ ይህንን ፈተና ለመጨረሻ ጊዜ አሁን እንሰጣለን። ከዚህ ፈተና ጋር የተዛመዱ የተጠያቂነት ግዴታዎች ወይም ሰበቦች በዚህ አመት የሉም።

ስለዚህ የሽግግር አመት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ የሆነውን መረጃ እባካችሁን በጥንቃቄ አንብቡት። ጥያቄ ካላችሁ፣ የልጃችሁን መምህር ወይም የት/ቤት ርእሰመምህር ከመጠየቅ አትቆጠቡ። በልጃችሁ ትምህርት በመጠመዳችሁና በመመሰጣችሁ አመስግናለሁ።

ከአክብሮት ጋር

Joshua P. Starr, Ed.D.
Superintendent of Schools
(የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ)

## የMaryland School Assessment (የሜሪላንድ ት/ቤት ግምገማ) (MSA) በማርች ወር 2014 ከ3ኛ እስከ 8ኛ ባሉት ክፍሎች በምንባብ/እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበባት እና በሂሳብ ይሰጣል።

ከማርች 3 እስከ 12 2014 ከ3ኛ እስከ 8ኛ ባሉት ክፍሎች ለሚገኙ አብዛኛዎቹ ተማሪዎቻችን በምንባብ/እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበባት (ELA) እና በሂሳብ ይሰጣል። ከ5ኛ እና 8ኛ የሚገኙ ተማሪዎች በተጨማሪ በማርች መጨረሻ ወይም በኤፕሪል መጀመርያ ላይ MSA በሳይንስ ይወስዳሉ። MSA በምንባብ/ELA እና በሂሳብ የሚሰጥበት ይህ የመጨረሻው አመት ነው። በሚመጣው አመት በPartnership for Assessment of Readiness for College and Careers (ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት የግምገማ ሽርክና) (PARCC) በነዚያ ርእስ ዙርያዎች ይተካል።

## አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ከሞላ ጎደል ከሁሉም ት/ቤቶች (ቢያንስ አንድ የመማርያ ክፍል በአንድ ርእስ) የሜሪላንድን አዲሱን የPARCC ግምገማዎች የመስክ ፈተና ይወሳዳሉ።

የሚመጣው አመት፣ ከCommon Core State Standards (የጋራ ዋነኛ የስቴት መመዘኛዎች) (CCSS)፣ በተጨማሪም Maryland College and Career-Ready Standards (የሜሪላንድ ኮሌጅና ስራ-ዝግጁ መመዘኛዎች) ተብሎ ከሚታወቀው፣ ጋር የተቃኙትን አዲሶቹን ስቴት-አቀፍ ግምገማዎች ሜሪላንድ ተግባራዊ ያደርጋል። ለነዚህ አዲስ ፈተናዎች ለመዘጋጀት፣ ከሞላጎደል ከሁሉም ት/ቤቶች ቢያንስ አንድ የመማርያ ክፍል በነሲብ ተመርጦ በምንባብ/ELA ወይም በሂሳብ የPARCC ግምገማዎች የመስክ ፈተና እንዲወስድ ይደረጋል። የልጅዎ የመማርያ ክፍል በPARCC የመስክ ፈተና እንዲሳተፍ በነሲብ ተመርጦ እንደሆነ የልጅዎ ት/ቤት ያስታውቅዎታል። የPARCC ግምገማ የመስክ ፈተና የሚከናወነው በመስመር ላይና በውረቀት-ና-እርሳስ በሁለቱም ቅርፀቶች ነው። ልዩ ትምህርት ወይም English for Speakers of Other Languages (እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች) (ESOL) የሚወስዱ ተማሪዎች በዚህ የመስክ ፈተና ይካተታሉ። እነዚህ ተማሪዎች ከPARCC የፈተና መመርያ ጋር የሚጣጣሙ መገልገያዎች እንዲያገኙ ይደረጋል። ያንድ የልዩ ትምህርት ተማሪ Individualized Education Program (ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም) (IEP) በPARCC መመርያ መሰረት የማይፈቀድ መገልገያዎች የሚጠይቅ ከሆነ፣ በመገልገያዎቹ ለመወያየት ለIEP ስብሰባ ወላጆቹ ጥሪ ይደረግላቸዋል። ለESOL ተማሪዎች፣ መገልገያዎቹ ፈተናውን ለመጨረስ የተራዘመ ጊዜ፣ ለባለሁለት ቋንቋ መዝገበ ቃላት፣ እና፣ ለሂሳብ ፈተና ብቻ፣ የፀሀፊ እርዳታን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## የPARCC የመስክ ፈተና በአንድ የርእስ መስክ (በምንባብ/ELA ወይም በሂሳብ) የሚወስዱ ተማሪዎች MSAን በሌላ በተሞከረው መስክ ይወስዳሉ።

በፌደራል ህግ መሰረት ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች በየአመቱ በምንባብ እና በሂሳብ መፈተን አለባቸው። ለምሳሌ፣ ሂሳብ በPARCC የመስክ ፈተና የሚወስዱ ልጆች MSAን በሂሳብ እንዲወስዱ በስቴቱ አይጠየቁም። ቢሆንም፣ MSAን በምንባብ/ELA እንዲወስዱ ይፈለግባቸዋል።

## ወላጆች የያንዳንዱን ተማሪ የMSA ውጤቶች ግላዊ ዘገባ ማግኘታቸው ይቀጥላል።

የልጅዎን የMSA ውጤቶች ከዲስትሪክቱ ይቀበላሉ፣ ከሞላጎደል በሰመር ወቅት። የውጤት ዘገባዎች የያንዳንዱን ተማሪ የMSA አፈፃጸም ያሳያሉ፣ እንዲሁም የት/ቤቱን፣ የአካባቢውን የት/ቤት ስርአት፣ እና የስቴቱን አጠቃላይ የፈተና ውጤቶች።

## ወላጆች ስለልጃቸው በPARCC መስክ ፈተና አፈፃጸም ግላዊዊ ውጤቶች አያገኙም።

የመስክ ፈተናዎች መደበኛ ፈተናዎች አይደሉም። የተማሪ መልሶች የፈተና ጥያቄዎችን ጥራት ለመገምገም አገልግሎት ላይ ይውላሉ እንጂ ማርክ አይሰጣቸውም አይዘገቡምም። ሆኖም፣ ወላጆች ልጃቸው በMSA የወሰዳቸው ርእስ(ሶች) ዘገባዎች መቀበል ይቀጥላሉ።

Montgomery County Public Schools

# ስፕሪንግ 2014 የሜሪላንድ ስቴት ፈተና

# (Spring 2014 Maryland State Testing)

ፌብሩዋሪ 2014

ይቀጥላል

# FACT



ትርጉም Language Assistance Services Unit o Division of ESOL/Bilingual Programs o Office of Curriculum and Instructional Programs

## የሚመጣው አመት (2014–15 የትምህርት ዘመን)፣ ከ3ኛ እስከ 8ኛ የሚገኙ ሁሉም የሜሪላንድ ተማሪዎች በምንባብ/ELA እና በሂሳብ የPARCC ግምገማዎች ይወስዳሉ።

የPARCC ግምገማዎች ከCCSS ጋር የተሳሰሩ ስለሆኑ ተማሪዎች በኮሌጅና በስራ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፍልጓቸውን መሰረታዊ ሂሳዊ አስተሳሰብ እና ፕሮብሌም የመፍታት ችሎታዎችን ይለካሉ። በኮምፒውተር ላይ የተመሰረቱ ፈተናዎች እያንዳንዱ ተማሪ

ምን መማር ላይ እንደሚገኝ ወቅታዊ መረጃ ይሰጣሉ።

## ከPARCC የመስክ ፈተና የሚገኙ መረጃዎች የሚመጣው አመት ለሁሉም ተማሪዎች ከመሰጠታቸው በፊት ግምገማዎችን ጥራት ለመስጠትና ለማሻሻል አገልግሎት ላይ ይውላሉ።

የመስክ ፈተና "ፈተናን ለመፈተን" እድል ይሰጣል — ፈተናው እንዴት ደህና እንደሚሰራ ለማየት፣ የጥያቄዎችን ጥራት ለመወሰን፣ እናም በ2014–15 የትምህርት ዘመን ለሁሉም ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ማስተካከያ ለማድረግ። የፈተና-አዘጋጅዎች የፈተና ጥያቄዎች እንዲለኩ የተተለሙባቸውን እውቀትና ሙያዎች በተግባር ይለኩ እንደሆነ በተለይ ይመለከታሉ እንዲሁም ጥያቄዎቹ ዋጋ ያላቸው፣ አስተማማኝ፣ እና ርትአዊ መሆናቸውን ይጠይቃሉ። የመስክ ፈተናው ለተማሪዎች፣ ት/ቤቶች፣ እና ለአካባቢ የት/ቤት ስርአቶች አዲሶቹ ግምገማዎች በትምህርት ዘመን 2014-15 ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት እንዲተዋወቋቸው እድል ይሰጣቸዋል።

## የPARCC የመስክ ፈተና በሁለት ክፍሎች ይሰጣል።

Performance-Based Assessment (ባፈፃፀም-የተመሰረተ ግምገማ) (PBA) ከማርች 24 እስከ ኤፕሪል 11 2014 ይከናወናል። ምንባብ/ELA PBA ፅሁፍ ሲተነተን በውጤታማ አፃፃፍ ያተኩራል። የPBA ሂሳብ የሚያተኩረው ተጨባጭ ያልሆነ አስተሳሰብ፣ ትክክለኛነት፣ ፅንአት፣ እና የመሳርያዎች ስልታዊ አጠቃቀም የሚጠይቁ በርካታ-ደረጃ ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ሙያዎችን፣ ፅንሰ ሀሳቦችን፣ እና ግንዛቤዎችን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ነው። End-of-Year Assessment (የአመት-መጨረሻ ግምገማ) (EOY) የሚከናወነው ከሜይ 5 እስከ ጁን 6 2014 ነው። የምንባብ/ELA EOY ትኩረት የንባብ ግንዛቤ ላይ ነው። የሂሳብ EOY ሁሉም ተማሪዎች በማቴማቲክስ ቅልጥፍና ለማሳየት የሂሳብ ፅንሰሀሳባዊ ግንዛቤ በተጨማሪ እንዲያሳዩ ጥሪ ያደርግላቸዋል።

የመስክ ፈተና አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በPBA እና በEOY በሁለቱም አካሎች ይሳተፋሉ።

## የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችም በPARCC የመስክ ፈተናዎች በተጨማሪ ይሳተፋሉ።

በነሲብ የተመረጡ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በእንግሊዘኛ 9፣ እንግሊዘኛ 11፣ ጂዮሜትሪ፣ እና በአልጄብራ II የPARCC መስክ ፈተናዎች ይሳተፋሉ። በ2014–2015 ጀምሮ፣ የPARCC ግምገማዎች በአልጄብራ 1 እና በእንግሊዝኛ 10ም ይሰጣሉ።

## ስለ ፈተና ተጨማሪ ጥያቄ ካላችሁ፣ የልጃችሁን መምህር ወይም ርእሰ መምህር ጠይቁ።

በልጅዎ የመማርያ ክፍል እና ት/ቤት ምን በመካሄድ ላይ እንዳለ የላቀ መረጃ ይኖራቸዋል። ልጅዎ ስኬታማ እንዲሆን በበኩላችሁ ቤት ውስጥ ማድረግ ስለምትችሉት ሀሳቦች ሊያጋሯችሁ ይችላሉ።

## ስPARCCለ ግምገማዎች ተጨማሪ መረጃዎች እባካችሁ እነዚህን ጎብኙ፡-

ስለPARCC የመስክ ፈተና መረጃ፡- www.parcconline.org/field-test

የPARCC ድርጣብያ፡ www.parcconline.org

የPARCC ናሙና የፈተና ጥያቄዎች፡ www.parcconline.org/samples/item-task-prototypes